**ለአዲሲቷ ኢትዮጵያ የጋራ ንቅናቄ (አኢጋን)**

ሰኔ 1፣ 2004ዓም

# ሁሉም እንዲያውቀው!

## የአቶ ሽፈራው ሽጉጤን ጉብኝት አስመልክቶ ለሳስካችዋን ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት ግልጽ መልዕክት

**"የኢትዮጵያ ህዝብ ደረቅ ደም እያፈሰሰ ነው፤ ሕዝቡ አሰቃቂ ከሆነው ድህነትና ጉስቁልና ለመውጣት የፈለገውን ያህል ቢዳክርም የሕዝቡ ልፋት ከአገር ውስጥ ወደ ውጭ ከሚፈሰው ገንዘብ አንጻር ሲታይ ሽቅብ የመዋኘት ያህል እጅግ የከበደ ነው"[i]**

**ውድ ፕሬዚዳንት ፒተር ማኪኖን፤**

በኢትዮጵያ የደቡብ ክልል ከሚገኘው የሐዋሳ ዩኒቨርሲቲ ከፍተኛ ባለሥልጣናት ከሰኔ 3 እስከ ሰኔ 8 ኦፊሴላዊ ጉብኝት ለማድረግ ወደ ሳስካችዋን ዩኒቨርሲቲ እንደሚመጡ ለአዲሲቷ ኢትዮጵያ የጋራ ንቅናቄ መረጃው ደርሶታል፡፡ እንደሚታወቀው እርስዎ የሚመሩት ይህ ዩኒቨርሲቲ ከሐዋሳ ዩኒቨርሲቲ ጋር ያለው ግንኙነት ከ1989ዓም ጀምሮ የዘለቀ ሲሆን በካናዳ ካሉት የትምህርት ተቋማት በተለይ በግብርና አንጋፋ የሆነው ይህ ዩኒቨርሲቲ በእርሻ ልማት፣ በመሬት አስተዳደር፣ በተመጣጠነ ምግብ፣ በጤና እና በምግብ ዋስትና ዙሪያ ከትምህርት ጋር በተያያዘ መልኩ የሚያደርገው ዕርዳታ ሳይጠቀስ የሚታለፍ አይደለም፡፡

**ከእርስዎ ጋር በግል ካለን ትውውቅ በላይ እኔም የዚህ ዩኒቨርሲቲ የቀድሞ ምሩቅ እንደመሆኔና የቀድሞ የሳስካቱን ከተማ የረጅም ዓመታት ነዋሪ እንደመሆኔ በእርስዎ አስተዳደር ሥር የሚገኘውን የሳስካችዋን ዩኒቨርሲቲ በሁሉም መስክ የሚያደርገውን የሚያኮራ ተግባር በግሌ በመጥቀስ በጋራ ንቅናቄው ስም ላመሰግንዎት እወዳለሁ፡፡** በተለይም በእርሻው ክፍለኢኮኖሚ ከኢትዮጵያ ዩኒቨርሲቲ ጋር ግንኙነት በማድረግ ሁሉም ዓይነት የተፈጥሮ ኃብት እያላት በረሃብና የምግብ ዕጦት የምትታወቀውን ኢትዮጵያን ለመርዳት ይህ እርስዎ የሚመሩት ዩኒቨርሲቲ የሚያደርገውን ተግባር የጋራ ንቅናቄያችን የሚዘነጋው አይደለም፡፡

ለአዲሲቷ ኢትዮጵያ የጋራ ንቅናቄ (አኢጋን) **"ከጎሣ ይልቅ ለሰብዓዊነት ቅድሚያ እንስጥ"** በሚል መሪ ዓላማ በኢትዮጵያ የማኅበራዊ ፍትሕ እንዲሰፍን የሚታገል ከማንም ያልወገነ፤ በሰላማዊ ትግል የሚያምን፤ ሁሉንም ኢትዮጵያውያን የሚያቅፍና በበርካታ የዓለም ዙሪያ ቅርንጫፍ ያለው ድርጅት ሲሆን **እኔም ይህንን ንቅናቄ የመምራት ኃላፊነት እንዳለብኝ ሁሉ የእርስዎ ዩኒቨርሲቲ ረሃብን ለማስወገድ የሚሰጠው ዕርዳታና ድጋፍ በከንቱ የትም የወደቀ እንዳይሆንና በሙሰኞችና ወንጀለኞች እጅ ውስጥ እንዳይገባ ዩኒቨርሲቲው የሚያደርገውን ዕርዳታና ድጋፍ በተመለከተ ከአንድ ወገን ብቻ ሳይሆን ከሁሉም ባለጉዳዮች የተለያዩ ሃሳቦችን መቀበልና ማስተናገድ ይገባዎታል ለማለት እደፍራለሁ፡፡**

ክቡር ፕሬዚዳንት፤

የሐዋሳ ዩኒቨርሲቲ፣ ቦርዱ፣ አስተዳደሩ፣ የአካዳሚው አባላት እና የክልሉ አስተዳደር በአጠቃላይ በኢህአዴግ ሙሉ ቁጥጥር ሥር የሚገኝ ሲሆን የዚህ ድርጅትም መሪ የሆኑት አቶ መለስ ዜናዊ ከኢትዮጵያ ሕዝብ ከሰባት በመቶ የማይበልጠውንና አናሳ የሆነውን የትግራይ ሕዝብ ነጻ አወጣለሁ የሚለው ህዝባዊ ወያኔ ሓርነት ትግራይ (ህወሓት) የተሰኘውን የዘር ድርጅት ደርበው በመምራት በአሁኑ ጊዜ በኢትዮጵያ ከማዕከላዊ እስከ ክልልና መንደር ድረስ ከዚሁ ዘር በተውጣጡ ተባባሪዎቻቸውና ደጋፊዎቻቸው ቁጥጥር ሥር አገሪቷን አፍነው እየገዙ ይገኛሉ፡፡ ይህ ደግሞ የጋራ ንቅናቄያችን የሚናገረው ብቻ ሳይሆን አገር ያወቀው፤ ፀሐይ የሞቀው እውነታ ነው፡፡

የዚህ ትምህርት ተቋም የቦርድ ሊቀመንበር የሆኑት አቶ ሽፈራው ሽጉጤ የደቡብ ክልል ፕሬዚዳንትም ናቸው፡፡ በሌላ አነጋገር ሥልጣናቸው ከሳስካችዋን ገዢ ጋር በኩልነት ሊታይ ይችላል፡፡ ከላይ ለመጥቀስ እንደሞከርነው የአቶ ሽፈራው ክልላዊ አስተዳደር ከውጪ ሲታይ ከማንም ተጽዕኖ ነጻ የሆነ ቢመስልም በአቶ መለስ በዘር ላይ መሠረት ባደረገው አገዛዝ ፍጹም ቁጥጥር ሥር የሚገኝ ነው፡፡ በዚህም ምክንያት አቶ ሽፈራውም ሆኑ ሌሎች ኃላፊዎች በኢትዮጵያ ስለሚካሄደው ነገር መልካም መልካሙን በአኻዝ በማስደገፍ ውብ ስዕል እየሳሉ ፓርቲያቸው ተናገሩ የሚላቸውን እያሳመሩ ያቀርባሉ እንጂ እውነታውን ፈጽሞ አይናገሩም፡፡ በመሆኑም በአሁኑ ጉብኝትም በኢትዮጵያ ውስጥ ስላለው በተለይም ራሳቸው አቶ ሽፈራው በሚመሩት ክልል እየተከሰተ ያለውን ረሃብ፣ አፈና፣ ሰቆቃ፣ የመብት ረገጣ፣ እስራት፣ ግድያ፣ የመሬት ነጠቃ፣ የግዳጅ መፈናቀል፣ ወዘተ በተመለከተ እዚሁ ካናዳ ጥገኝነት የመጠየቅ ሃሳብ ከሌላቸው በስተቀር አንድም ቃል ትንፍሽ እንደማይሉ እሙን ነው፡፡

በአቶ መለስ እና በተባባሪቻቸው አቶ ሽፈራው አገዛዝ ሥር በምትገኘው ኢትዮጵያ የሚደርሰው የመብት ጥሰት በተመለከተ ለአዲሲቷ ኢትዮጵያ የጋራ ንቅናቄን[ii] ጨምሮ በርካታ የሰብዓዊ መብት ተሟጋች ድርጅቶች - Human Rights Watch[iii], Genocide Watch, Reporters without Borders[iv], Amnesty International, the Task Force on Financial Integrity and Development, the Committee for the Protection of Journalists, Survival International, the Oakland Institute የመሳሰሉ በርካታ ዓለምአቀፍ መ/ቤቶች መረጃዎችን በየጊዜው እያሰባሰቡ ይገኛሉ፡፡ በአሁኑ ጊዜ ግን በኢትዮጵያ የሚገኘው ሁኔታ እጅግ አሳሳቢ እየሆነ በመምጣቱ ከመረጃ ማሰባበሰብ ያለፈ ተግባር እየተከናወነ ሲሆን የተለያዩ አፋኝ ሕጎችን በማውጣት፣ ተቃዋሚዎችን ሁሉ ‹‹አሸባሪ›› በማለት ዜጎችን መተንፈሻ ያሳጣው ይህ አገዛዝ ለፍርድ የሚመጣበት ጊዜ ሩቅ እንደማይሆን ሁኔታዎች እየጠቆሙ ይገኛል፡፡ የአፈናውም ሁኔታ በተለያየ መልኩ እየተካሄደና እየተጠናከረ ሲሆን ባለፈው ወር የጋራ ንቅናቄያችን "አዲሱ ቴሌና ኢንሳ፡ የህወሓት/ኢህአዴግ የስለላ መረብ"[v] በሚል ርዕስ ባወጣው 47 ገጽ ዘገባ መሠረት የአገዛዙን የስለላ መ/ቤት ከቻይና በተገኘ ቴክኖሎጂ ከቴሌ ጋር በማቆራኘት በአገር ውስጥና ከውጪ የሚካሄዱትን የመረጃ ፍሰቶች ለመቆጣጠርና ለማፈን የታቀደውን በተወሰነ መልኩ ዘግበናል፡፡

ይህ ብቻ አይደለም በኢትዮጵያ ውስጥ በከፍተኛ ሁኔታ እየተስፋፋ የመጣውን ሙስና አስመልክቶ የተለያዩ መረጃዎች እንደሚጠቁሙት ለዕርዳታ ከውጪ የሚመጣን ገንዘብ አገዛዙ የራሱን ሥልጣን ማራዘሚያነትና የተቃዋሚዎችን እንቅስቃሴ ለማፈን እየተጠቀመበት መሆኑንና በውጤቱም ከ1992 እስከ 2001ዓም ባሉት ዓመታት 11.3 ቢሊዮን ዶላር በሙስና፣ በስርቆት፣ በጉቦና በህገወጥ መንገድ ገንዘብን በማስተላለፍ ከአገር እንደወጣ the Task Force on Financial Integrity and Development ባወጣው ጥናታዊ መረጃ ላይ ዘግቧል[vi]፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘም መሬታቸውን "ለልማት ይፈለጋል" እየተባሉ የተነጠቁ ከ70ሺህ በላይ ገበሬዎች ከመኖሪያ ቀያቸው ተፈናቅለው መግቢያ ያጡበትም ሁኔታ በቅርብ ጊዜያት ከተከሰቱት ወንጀሎች አንዱ ነው፡፡ ይህንኑ ጉዳይ አስመልክቶ Human Rights Watch በሰፊው ባተተው ዘገባው ላይ በግልጽ አስፍሯል[vii]፡፡

በአሁኑ ጊዜ በሥልጣን ላይ ያለው የህወሓት/ኢህአዴግ አገዛዝ የድርብ አኻዝ የኢኮኖሚ ዕድገት በኢትዮጵያ አስመዝግቤአለሁ፤ ኢትዮጵያ በፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት ላይ ትገኛለች፤ ወዘተ

**ቢልም እስካሁን ዓመታዊውን በጀት የሚደጉመው ከምዕራባውያን በሚያገኘው ዕርዳታና ድጎማ መሆኑን ራሱ አገዛዙ በየጊዜው የሚያወጣው መረጃ በቂ ማስረጃ ነው፡፡ በዓለም አቀፍ ደረጃ ብልጽግናን፣ የኢኮኖሚ ዕድገትን፣ የግል ሃብትን እና የኑሮ ብቃትን እንደ መስፈርት በማድረግ የተለያዩ አገራትን ደረጃ የሚያወጣው** Legatum Institute **የተሰሰኘው ተቋም ባለፈው ዓመት ባደረገው መለኪያ መሠረት ከ110 አገራት ውስጥ ኢትዮጵያ በነሱዳንና ሌሎች የአፍሪካ አገራት ተበልጣ በ108ኛ ደረጃ ላይ እንደምትገኝ ዘግቧል፡፡**[viii] ከዚህ በተጨማሪም በሌሎች ዓለምአቀፋዊ መስፈርቶች ማለትም በኢንተርኔት አጠቃቀም፣ በተንቀሳቃሽ ስልክ፣ በማኅበራዊ መስተጋብር፣ በመሳሰሉ የቴክኖሎጂ ውጤቶች በጦርነት ከተበጣጠሰችው ሶማሊያ በታች እንደምትገኝ በርካታ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡

የአቶ መለስ አገዛዝ በኢትዮጵያ ነጻነት እንዳይኖርና ሕዝቡ መብቱን እንዳይለማመድ የሚያደርገውን አፈና በመቀጠል **መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን**[ix] **የሚያፍንበት ሕግ፣ ተቃዋሚ እንቅስቃሴዎችን የሚያስፈራራበትን የጸረ ሽብርተኝነት ሕግ በማውጣት ያደረገው አፈና አልበቃ ብሎት በቅርቡ ደግሞ የማተሚያ ቤቶች ማንኛውንም ጽሁፍ ከማተማቸው በፊት የራሳቸውን ሳንሱር እንዲያደርጉ ሕግ በማውጣት የአፈናውን ገመድ አክርሮታል፡፡**

**ክቡር ፕሬዚዳንት፤**

በቅርቡ በሃይማኖት ዙሪያ የህወሓት/ኢህአዴግ አገዛዝ እያደረገ ያለው የመከፋፈል ድራማ ምን ያህል የአንድነት ጸር መሆኑን ብቻ ሳይሆን ተስፋ መቁረጡን በግልጽ የሚያሳይ ማስረጃ ነው፡፡ **ለዘመናት የኖሩ በታሪክና ዓለምአቀፋዊ ቅርስነት የሚጠቀሱትን እንደ ዋልድባ ያሉትን ገዳማትንና አብያተክርስቲያናትን ማፍረስ፣ ተዋድዶና ተፋቅሮ የኖረውን የሙስሊምና ክርስቲያን ሕዝብ እርስበርስ ማናቆር፣ በሙስሊሙ ኅብረተሰብ ውስጥ ካድሬዎቹን ማሰማራትና የመጅሊስን አመራር መቆጣጠር፣ ጽንፈኛ አስተምህሮት በመስጊድ ማስፋፋት፣ ወዘተ ከሚጠቀሱት ጥቂቶቹ ናቸው፡፡** ይህም አልበቃ ብሎት ከስድስት ሳምንታት በፊት **"የሃይማኖት መብታችን ይከበር"** በማለት ጥያቄ ያነሱትን ሙስሊሞች በመስጊዳቸው ውስጥ ከአገዛዙ የተላኩ ታጣቂዎች ተኩስ በመክፈት **ከ17 በላይ ሙዕሚኖችን ሲገድሉ ከመካከላቸውም የ6ዓመት ህጻን አንዱ መሆኑ የጭከናውን ለከት ማጣት በግልጽ የሚመሰክር ነው፡፡**

**ወደ ሳስካችዋን ዩኒቨርሲቲ የሚመጣው የአቶ ሽፈራው ቡድን በራሱ አስተሳሰብ የሚንቀሳቀስ፣ የሕዝብን ጥቅም የሚያስከብር በተለይም የአካዳሚ ነጻነትን የተጎናጸፈ ቡድን ሳይሆን ከላይ እንደጠቀስኩት በአቶ መለስ በሚመራው የትግራይ ነጻአውጪ ግምባር ሳንባና አፍንጫ የሚተነፍስ ነው፡፡ ከጥቂት ወራት በፊት ራሳቸው አቶ ሽፈራው በፈረሙት ደብዳቤና በሰጡት ትዕዛዝ**[x] **ራሳቸው በሚመሩት የደቡብ ክልል ውስጥ በጉራፋርዳ ለበርካታ ዓመታት ንብረት አፍርተውና ወልደው ከብደው ይኖሩ የነበሩ 70ሺህ የአማራ ተወላጆችን ያለአንዳች ሃብትና ንብረት እንደ ለማኝ ፌስታል አንጠልጥለው እንዲባረሩ፤ ተማሪዎችን ከትምህርት ገበታቸው ተፈናቅለው ከክልሉ እንዲለቁ ማስገደዳቸው የዘር ፖለቲካን በሚያራምደው የህወሓት መዳፍ ሥር ለመሆናቸው አጠያያቂ ያልሆነ ማስረጃ የሰጠ ተግባር ነው፡፡** ሁኔታው ይፋ ሆኖ አቶ ሽፈራው ስለጉዳዩ ሲጠየቁ **"እንድም የተፈናቀለ ሰው የለም"** በማለት ድርጊቱን ቢክዱም ከጉራፋርዳ የተፈናቀሉት ወገኖቻችን ሲቃ እየተናነቃቸው አገር አልባ መደረጋቸውን በአንደበታቸው መመስከራቸውን የአሜሪካን ድምጽ ሬዲዮን ጨምሮ የሪፖርተር ጋዜጣና የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት በስፋት ዘግበውታል፡፡

እንዲህ ያለውን አስገድዶ ማፈናቀልና ከመኖሪያ ቦታ የማስነሳት ተግባር በዓለምአቀፍ ሕግጋት የተወገዘ መሆኑንና "የሮም ሕገደንብ" (Rome Statute) ተብሎ በተለይ በሚታወቀው ዓለምአቀፉ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ አንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ (መ) ላይ የተደነገገ ነው፡፡ አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ (መ) ደግሞ **"ከመኖሪያ ቦታ ማፈናቀል ወይም ሕዝብን በግዳጅ ከመኖሪያ ማዛወር"** የሚለውን ሲተነትን **"ኃይልን በመጠቀም፣ በማስገደድ ወይም አስገዳጅ ድርጊቶችን በመጠቀም ሰዎችን ሕጋዊ ሆነው ከሚኖሩበት ቦታ ዓለምአቀፍ ሕግ ከሚፈቅደው ውጪ ማስነሳት፣ ማባረር . . ."** ማለት ነው ይላል፡፡ ህወሃት/ኢህአዴግ "ኢትዮጵያ የዓለምአቀፍ ህግጋትን ትቀበላለች" በማለት በውጪው

ኅብረተሰብ ዘንድ በሕግ የበላይነት የሚያምን መስሎ ለመታየት ሙከራ ቢያደርግም "የዓለምአቀፍ ህግጋትን መቀበል" ብቻ ከጥፋተኝነት አለማዳኑን እያወቀ ጥፋት በሚፈጽም ላይ ቅጣቱ እንደሚከብድበት ከአቶ መለስ ጀምሮ እስከ ክልል የሚገኙት ባለሥልጣናት የሚዘነጉት አይደለም፡፡

**አቶ ሽፈራው በሚመሩት ክልል ውስጥ በኦሞ ሸለቆ የሚገኙት ከ50ሺህ በላይ ነዋሪዎችም በአካባቢው በሚገነባው የጊቤ III ግድብ ምክንያትና አሁን በተያዘው የማፈናቀል ፖሊሲ ሰለባ እንደሚሆኑ ይጠበቃል፡፡ ይህ ብቻ አይደለም ይህ ግድብ በሥራ ላይ በሚውልበት ጊዜ ከ500ሺህ በላይ የሚሆኑትን ከመላው ኢትዮጵያ ህዝብ እጅግ የተገለሉትና የተረሱትን ዜጎች ሕይወት ፍጹም አደጋ ላይ የሚጥል ይሆናል፡፡[xi] የሁኔታውን አሳሳቢነት በመረዳትም የአውሮጳ ኅብረትና የዓለም ባንክ ፕሮጀክቱን ከመደጎም ቢታቀቡም ህወሓት/ኢህአዴግ ሌሎች የብድር ዘዴዎችን በመጠቀም በዕቅዱ ገፍቶበት ይገኛል፡፡**

**ክቡር ፕሬዚዳንት ማኪኖን፤**

እርስዎ በሚመሩት ዩኒቨርሲቲ የሚገኙት ምሁራንና ተማሪዎች በኢትዮጵያ ዩኒቨርሲቲዎች ውስጥ የሚካሄደውን የአካዳሚ መብት ገፈፋ በውል ሊያውቁት የሚገባ ተግባር እንደሆነ አምናለሁ፡፡ ይህ በዘርና በፖለቲካ አባልነት መዘውር የሚንቀሳቀሰውን የአካዳሚ ኅብረተሰብ አስመልክቶ ግንቦት 30፤2004ዓም የወጣው የአሜሪካ ውጭ ጉዳይ መ/ቤት የሰብዓዊ መብት ዘገባ ይህንኑ ሐቅ በማስረጃ መዘገቡ ሌላው ሊጠቀስ የሚያሻው ነው፡፡ **"በኢትዮጵያ የሥርዓተ ትምህርቱ፣ የመምህራን ሹመት፣ የተማሪዎች ወደ ከፍተኛ ትምህርት ተቋም የመግባት ውሳኔ በሙሉ በመንግሥት ቁጥጥር ሥር ይገኛል፡፡ በከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችና በዩኒቨርሲቲዎች ውስጥ የመናገር፣ ሃሳብን የመግለጽና የመሰብሰብ መብቶች ዕገዳ ተጥሎባቸዋል፡፡ በትምህርት ተቋማት የኢህአዴግ አብዮታዊ ዴሞክራሲ ጽንሰሃሳብ ተማሪዎች እንዲማሩ ይደረጋሉ፡፡ ታማኝ የሆኑ ምንጮች እንደሚሉት በአገሪቷ ከሚገኙት ትልቁ በሚባለው የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የገዢውን ፓርቲ ርዕዮተዓለም የሚያስተጋብሩና ወደፊት ሊከሰቱ የሚችሉ ተቃውሞዎችን ሊከላከሉ የሚችሉ 'ታማኞች' በዩኒቨርሲቲው እንዲበራከቱ እየተደረገ ነው፡፡ መንግሥት የአካዳሚ ነጻነትን በተለያዩ ዘዴዎች በመገደብ መምህራን ካወጡት የትምህርት ዕቅድ ውጪ ምንም ዓይነት ፖለቲካዊ መሰል እንቅስቃሴዎችን ከማድረግ የተከለከሉ ሲሆን የተለያዩ ዘገባዎች እንደሚያስረዱት የኢህአዴግ አባል ያልሆኑ መምህራን ወደማይፈልጉበት ቦታ እንዲዛወሩ እንዲሁም ዕድገት እንዲያልፋቸው እንደሚደረግ ይመሰክራሉ፡፡ መምህራን በእውቀታቸው ብቻ ሳይሆን በተለይ የዘር ሃረጋቸው ተመዝኖ፣ የፓርቲ አባልነታቸው ተጣርቶ፣ የሃይማኖት መደባቸው ተመርምሮ የአቀጣጠርና የአመዳደብ ሁኔታቸው እንደሚወሰን በየጊዜው የሚቀርቡት አቤቱታዎች ማስረጃ ናቸው፡፡ በአንዳንድ ኮሌጆች ተማሪዎች ለመመዝገብ ይችሉ ዘንድ እንዲሁም ከምረቃ በኋላ በመንግሥት ተቋማት ውስጥ ሥራ ለማግኘት ለኢህአዴግ ያላቸውን ታማኝነት እንዲገልጹ ተጽዕኖ ይደረግባቸዋል፡፡ ሌሎች በርካታ ታማኝ ምንጮች እንደሚሉት ደግሞ መምህራንና ከ10ኛ ክፍል በላይ የሚገኙ ተማሪዎች የአብዮታዊ ዴሞክራሲን ጽንሰሃሳብና የኢህአዴግን ርዕዮተዓለም በሥልጠና መልክ እንዲከታተሉ የሚጠበቅባቸው መሆኑን የገገጹ ሲሆን በርካታ ተማሪዎች ወደ ዩኒቨርሲቲ ለመግባት የኢህአዴግ አባል መሆን አስፈላጊነት እንደሚያምኑበት ከዩኒቨርሲቲ ምረቃ በኋላም በአባልነት እንደሚቀጥሉ ተናግረዋል፡፡ በትምህርት በሚቆዩበት ጊዜም ተማሪዎች የሚያገኙት ከ A እስከ D ያለው የትምህርት ውጤታቸው የሚወሰነው ታማኝነታቸው ተለክቶና ከትክክለኛው ዘር መሆናቸው ተጣርቶ መሆኑን" ዘገባው በግልጽ አስቀምጧል፡፡**[xii] እንዲህ ባለው አስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ የሚገኙ ተማሪዎችና መምህራን አገራቸውን እየለቀቁ ካናዳን ጨምሮ ወደተለያዩ አገራት ለመሰደድ ተገድደዋል፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ ከየካቲት 5 ቀን እስከ የካቲት 11 ቀን 2004 ዓም ድረስ የደቡብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥትን የሚመራው የደቡብ ኢትዮጵያ ህዝቦች ዴሞክራሲያዊ ግንባር (ደኢህዴን) የከፍተኛ አመራር ግምገማ ባካሄደበት ወቅት አሁን የእርስዎን ዩኒቨርሲቲ ሊጎበኙ የሚመጡት የክልሉ ፕሬዚዳንት አቶ ሽፈራው ሽጉጤ ጠንካራ ግምገማ ተካሂዶባቸው ነበር፡፡ **የሲዳማ ቡና ላኪዎች ማህበር አባልና በማህበሩ ከፍተኛ ባለአክሲዮን እንደሆኑ በግምገማ የቀረበባቸው አቶ ሽፈራው፣ በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠር ገንዘብ መዝብረዋል በሚል ጠንካራ አውጫጪኝ ተካሂዶባቸዋል።**

በኢህአዴግ የፖለቲካ ቋንቋ አቶ ሽፈራው ሽጉጤን በ“ኪራይ ሰብሳቢነትና በሙሰኝነት” ተፈርጀው ነበር። በቀጣዩም ፕሬዚዳንቱ ከሥልጣን ወርደው በህግ እንዲጠየቁ ድርጅታዊ ውሳኔ ሲበየንባቸው፣ “እኔ ብቻዬን አይደለሁም፣ ከጠቅላይ ሚኒስትሩ ባለቤት ወይዘሮ አዜብ መስፍን ጋር በጋራ ገንዘቡን ወስደናል፡፡ የምንጠየቅም ከሆነ ሁለታችንም በህግ ፊት መቅረብ አለብን፡፡ ብሩን መመለስም ካለብን ሁለታችንም እንመልስ” በማለት የግምገማ መድረኩን ረግጠው መውጣታቸው በስፋት የተዘገበ ክስተት ነበር። በእንዲህ ዓይነት ሁኔታ በግልጽ ሙሰኛ ለመሆናቸው የተረጋገጠባቸው በቦርድ ሰብሳቢነት ለሚመሩት ዩኒቨርሲቲ የእርስዎ ዩኒቨርሲቲ የሚያደርገው የገንዘብ ድጎማና ድጋፍ የት እንደሚደርስ መገመት የሚያዳግት አይደለም፡፡

የሐዋሳ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት የሆኑት ዶ/ር ዮሴፍ ማሞ ዱባለ እንዲሁ በክልሉ በተካሄደ መጠነሰፊ ሙስና ውስጥ እጃቸው እንዳለ በማስረጃ ቢረጋገጥም የእርሳቸውም ክስ እንደ አቶ ሽፈራው በበላይ አመራር ውድቅ ተደርጓል፡፡ ከላይ እንደጠቀስኩት በከፍተኛ ሙስና ውስጥ የተዘፈቁት እነዚህ ከፍተኛ የዩኒቨርሲቲው አመራሮች ከካናዳ ግብር ከፋይ ኅብረተሰብ በእርስዎ ዩኒቨርሲቲ እንዲሁም በካናዳ የዓለምአቀፍ ልማት ኤጀንሲ (CIDA)፣ የዓለምአቀፍ ልማት ጥናት ተቋም (IDRC)፣ የካናዳ የዩኒቨርሲቲና ኮሌጆች ማኅበራት (AUCC) አማካኝነት የሚደረገው የፕሮጀክት ማስፈጸሚያ ዕርዳታና ድጎማ ልዩ አትኩሮት ሊሰጠው የሚገባ ተግባር መሆኑን ለማስገንዘብ እወዳለሁ፡፡ ከዚህም አልፎ በአፍቃሪ ኢህአዴግነቱ የሚታወቀው የአዲስ ፎርቹን ጋዜጣ እንኳን ሳይቀር በግንቦት 19 ዕትሙ “አብዮታዊ ዴሞክራሲ ያስርባል” በሚል ርዕስ ባወጣው ሃተታ ላይ አቶ መለስ በዓለምአቀፍ መድረኮች ላይ የኢትዮጵያን ዕድገት ቢሰብኩም አቶ ሽፈራው የሚመሩት አረንጓዴው የደቡብ ክልል ግን በረሃብ እየተንገላታ መሆኑ እንደሚያጠያይቅ የሰላ ሂሱን ሰንዝሯል፡፡[xiii]

በመሆኑም የሳስካችዋን ዩኒቨርሲቲና እርስዎ ከላይ ለዘረዘርኳቸው እጅግ አጠያያቂ የሆኑ የሰብዓዊ መብት ረገጣዎችና የሙስና ተግባራት “አልሰማሁም፤ አላየሁም” ማለት እንደማይገባው ላሳስብዎት እፈልጋለሁ፡፡ ወደ ኢትዮጵያ ፈሰስ የሚደረገው ገንዘብ ግልጽነትና ተጠያቂነት ሊኖረው እንደሚገባ አፈጻጸሙም በተገቢው ቦታ ላይ መዋሉ ሊመረመር ይገባዋል ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ፡፡ በኢትዮጵያ ከሚገኝ ማንኛውም ተቋም ጋር የሚደረግ ትብብር በጥንቃቄ ሊወሰድና ይህ ዩኒቨርሲቲም በመተዳደሪያው በግልጽ እንዳሰፈረው ለሕጉና ለመላው የአካዳሚ ኅብረተሰብ ተገዢ መሆን ይገባዋል፡፡ ከሌሎች ጋር በሚያደርገው የዕርዳታ ስምምነት የወንጀል ተባባሪ ከመሆን በመቆጠብ እንዳለበት ለማሳሰብ እወዳለሁ፡፡ ይህ ደግሞ ለዩኒቨርሲቲው ብቻ ሳይሆን በዓለምአቀፍ ተራድዖ ላይ ለተሰማሩት የካናዳ ድርጅቶችም መሆኑን የዚህን ደብዳቤ ግልባጭ እንዲደርሳቸው በማድረግ ፖሊሲያቸውን እንደገና እንዲመረምሩ ልናስገነዝባቸው እንወዳለን፡፡

በኢትዮጵያዊ ካናዳዊነቴና ከህይወቴ ግማሽ በላይ የሆነውን ጊዜ በሳስካቱን ከተማ ማሳለፌ ወደፊት ለማስባት አዲሲቷ ኢትዮጵያ መሠረት እንድጥል ያደረገኝና የታነጽኩበት ነው፡፡ ከተማርኩበት ዩኒቨርሲቲ ጀምሮ በአጠቃላይ ከከተማው ሕዝብ ጋር ያለኝ ትውውቅ በርካታ ትዝታዎችን ጥሎብኝ ያለፈ ብቻ ሳይሆን ከፍተኛ ትምህርትንም ያስተማረኝ ነው፡፡ አሁንም ይህንን ዓይነቱን ድርጊት ለእርስዎ ሳሳውቅዎት ከዚህ በመነሳት መሆኑን እንደሚያስተውሉትና ወደፊትም ለሰብዓዊ ዘር በሚደረገው መልካም ተግባር ተባባሪዎች ሆነን እንደምንቀጥል ተስፋ በማድረግ ነው፡፡

ከምስጋና ጋር፤



አባንግ ሜቶ
ለአዲሲቷ ኢትዮጵያ የጋራ ንቅናቄ
ዋና ዳይሬክተር

2-315 Frank Street
Ottawa, Ontario K1P 0X1
Canada
Email: Obang@solidaritymovement.org

ግልባጭ፤
የካናዳ የዓለምአቀፍ ትብብር ሚኒስትር የተከበሩ ቤቨርሊ ጄ ዖዳ
የዓለምአቀፍ ልማት ጥናት ማዕከል (IDRC) ፕሬዚዳንት ዴቪድ ኤም ማሎን
የካናዳ ዩኒቨርሲቲዎችና ኮሌጆች ማኅበር (AUCC) ፕሬዚዳንት ፖል ዴቪድሰን

ከዚህ በተጨማሪ ይህ መልዕክት ለሳስካችዋን ዩኒቨርሲቲ ምክትል ፕሬዚዳንቶች፤ ለእርሻ፣ ለሕዝብ ጤና፣ ለሕዝብ ፖሊሲ፣ ለሕክምና፣ ለፋርማሲና ምግብ፣ ለነርሶች ማሰልጠኛ፣ ለከብት ሕክምና፣ ለጥርስ፣ ለቢዝነስ፣ ለሥነ ጥበብና ሳይንስ ኮሌጅ ዲኖችና ምክትል ዲኖች እንዲሁም በአጠቃላይ ከ300 መቶ በላይ ለሚሆኑ የዩኒቨርሲቲው መምህራን በየኢሜይል አድራሻቸው እንዲደርስ ተደርጓል፡፡

ዋቢ

---

[i] (Global Financial Integrity የተሰኘው ተቋም ያለአግባብ ከኢትዮጵያ እየተመዘበረ ስላለው በቢሊዮን ዶላር የሚቆጠር ሃብት ከዘገበው የተወሰደ፡፡)
[ii] http://www.solidaritymovement.org/110608PressReleasesOnJointReport.php; Joint Report from Oakland Institute and SMNE Sounds Alarm on Foreign Agri-Investments in Food Insecure Ethiopia
[iii] http://www.hrw.org/reports/2010/10/19/development-without-freedom-0; Development Without Freedom: How Aid Underwrites Repression
[iv] http://allafrica.com/stories/201112220365.html Letter from Reporters Without Borders to UN Special Rapporteur on Abuse of Anti-terrorism Law
[v] http://www.solidaritymovement.org/amharic/120419TeleandINSAIntro.php
[vi] http://www.financialtaskforce.org/2011/12/05/illicit-financial-outflows-from-ethiopia-nearly-doubled-in-2009-to-us3-26-billion-reveals-new-global-financial-integrity-report/
[vii] http://www.hrw.org/reports/2012/01/16/waiting-here-death
[viii] http://www.prosperity.com/country.aspx?id=ET ; 2011 Legatum Prosperity Index
[ix] http://www.civicus.org/csw_files/CIVICUSAnalysisEthiopiaCharitiesProc160908.pdf; The 2009 Charities and Societies Proclamation prohibits any organization that receives more than 10% of its budget from foreign sources from (a) advancing human and democratic rights, (b) promoting equality of nations, nationalities, peoples, gender and religion, (c) promoting the rights of the disabled and children, (d) promoting conflict resolution or reconciliation and, (e) promoting the efficiency of justice and law enforcement services.
[x] http://www.zehabesha.com/?p=5340
[xi] http://www.survivalinternational.org/news/8115
[xii] http://www.state.gov/j/drl/rls/hrrpt/humanrightsreport/index.htm?dynamic_load_id=186196
[xiii] http://www.addisfortune.net/Revolutionary%20Democracy%20Starves.htm